# ገብረ ክርስቶስ ደስታ፡ ገጣሚ-ሰዓሊ? ወይስ ሰዓሊ-ገጣሚ?

## በሚል ርእስ፤ የጀርመን ካልቸራል ኢንስቲትዩት እና ፈቃደ አዘዘ ባዘጋጁት የግጥም ጉባዔ ላይ፥ ጥቅምት 12 ቀን 1996፥ ፈቃደ ያደረገው የመግቢያና የፕሮግራም ማስተዋወቂያ ንግግር

ከጀርመን የባህል ኢንስቲትዩት ጋር እንደ ዛሬው ዓይነት የግጥም ንባብ ፕሮግራም ስናዘጋጅ ስድስተኛችን ነው፡፡ ኅዳር 19 ቀን 1995 በፈቃደ አዘዘ ጀመረ፥ በዮናስ አድማሱ፥ በደበበ ሰይፉ፥ በሰይፉ መታፈሪያ፥ እና ስማቸው ባልታወቀው የገበሬ ገጣሚዎች ቀጥሎ እዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ የፕሮግራሙ አዘጋጅ (ፈቃደ አዘዘ) ስለኢትዮጵያ ስነፅሁፍ ተምርምር ሙከራው ባገኘው መጠነኛ እውቀት፥ በራሱ መመዘኛ እና ጣጥሚያ (taste) የመሰለውን እየመረጠ ለማቅረብ ያለው ነፃነት ለጥቂት ጊዜ ቢቀጥል መልካም ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ሌላ ሰው በተመሳሳይ መንገድ እንዲያዘጋጅ ቢደረግ የሀገሪቱም ሆነ የከተማችን የስነፅሁፍ ሕይወት ይበለፅጋል ብዬ አስባለሁ፡፡ እኔ ግን ለጊዜው ደርዘን ብሞላ ደስ ይለኛል፡፡

ዛሬ ቀኑ የአቶ ገብረ ክርስቶስ ነው፡፡ አቶ ገብረ ክርስቶስ ደስታን በግል አላውቀውም፡፡ በዚህ በጣም አዝናለሁ፥ እቆጫለሁም፡፡ ዋናው ምክንያት፥ እስከ ዛሬ በየሕይወት መስኩ መላ ያልተገኘለት የትውልድ ክፍተት ፕሮብሌም እንደነበር ስረዳ ደግሞ እበግናለሁ፡፡ ይህ እራሱን የቻለ ውይይት የሚፈልግ ስለሆነ በዚሁ ልግታውና ስለ አቶ ገብረክርስቶስ ወደ ጀመርኩት ወግ ላቅና፡፡ ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ በቀጥታ፥ ግን በጣም እሩቅ ቦታ አዳራሹ ውስጥ ቆሜ የሰማሁትና ተንጠራርቼ ያየሁት፤ እርሱ፥ አቶ ሰለሞን ዴሬሳ፥ አቶ ጸጋዬ ገብረ መድኅን፥ አቶ ሰይፉ መታፈሪያ፥ አቶ መንግስቱ ለማና አቶ ዓለማየሁ ሞገስ በአቶ (ዛሬ ፕሮፌሰር) መስፍን ወልደ ማርያም አጋፋሪነት፤ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፥ በስድስት ኪሎ ቅፅረ ግቢ በሚገኘው በራስ መኮንን አዳራሽ ግጥም ያነበቡ ጊዜ ነበር፡፡ ዛሬ ሳስበው፥ ያንን የመሰለ የግጥም ንባብ መድረክ በሀገሪቱ ውስጥ እስከዛሬ ድረስ፥ በድጋሚ ተዘጋጅቶ የሚያውቅ አይመስለኝም፡፡ ገጣሚዎቹ ስለስነፅሁፍ ምንነት፥ ስለፅነፅሁፍ ተግባርና ስለ ደራሲው ሚና የተለያየ አስተያየት የነበራቸው፥ በእውቀትና በምግባራዊ ድፍረት በየራሳቸው እግር መቆም የሚችሉ ነበሩ፡፡ ምንም እንኳ መድረኩ የግጥም ማንበቢያ ብቻ ቢነብርም፤ እነዮሐንስ አድማሱ በትውርና በግብር ይወክሉት የነበረው ድምፅ እግጥም ንባቡ ላይ ቀጥተኛ ወኪል ባይነብረውም፤ በዚያን ዘመን በሀገሪቱ ውስጥ የነበረውን

የስነፅሁፍ አዝማሚያ ከሚጠቁሙት አስተያየቶች ብዙዎቹ የተወከሉበት መድረክ ነበር። ዩኒቨርሲቲው እንደገና ሊያስብባቸው ከሚገባው፣ ከመደበኛ ትምህርት ጎን ለጎን የምር፣ በስፋት (በየካምፐሱ ማለቴ ነው) መኪያሄድ ካለባቸው እንቅስቃሴዎች አንዱ ነው። ዎሌ ሾይንካ በተሸለመበት የኡዝዋ ታሪካዊ መድረክ ላይ፣ የሽልማቱ አዘጋጂዎች፣ በነካ እጃቸው፣ በሬድዮና በቴሌቪዥን እንደ ሽልማቱ ስነስርዓት በነፃና በቀጥታ የሚተላለፍ ብሄራዊ የግጥም ንባብ ቢያዘጋጁ፤ ሾይንካ የተሸለመው እውነትም በጥበባዊ ምክንያት ብቻ ለመሆኑ አንድ ማረጋገጫ ይሆናል፤ ለሀገሪቱ ስነጽሁፍም አንድ የዩኒቨርሲቲ ሽልማትና ለወጣት ገጣሚዎችም ተጨማሪ ማነቃቂያ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። በነገራችን ላይ፣ እንዲህ ዓይነቱን ዝግጅት፣ ወይም እርሱን መሰል ዝግጅት በማዘጋጀት እስከ ዛሬ ለመታከታቸው ጉልህ የስራ ምስክር ካላቸው ሰዎች ጋር ሆኖ፣ ከዚህ በላይ የጠቀስኩትን "ብሔራዊ የግጥም ጉባዔ"፣ እደግመዋለሁ "ብሔራዊ የግጥም ጉባዔ" በፍፁም ነፃነት ለማዘጋጀት ከተፈቀደና መጠነኛ (የአሻሮ መግዣ ያህል) ወጭም ከተመደበ በእንዲህ ዓይነቱ ትልቅ ፋይዳና ክብር ባለው ዝግጅት ውስጥ ለመካፈል በበኩሌ በጣም ፈቃደኛ ነኝ።

አቶ ገብረ ክርስቶስን መነሻ አድርጎ፣ በትዝታ መልክ ወደተቀሰቀሰብኝ ሀሳብ መንፈሴ በመሸፈቴ ይቅርታችሁን እጠይቃለሁ። ጉዳዩ ከብዙ የባህል፣ የስነጥበብ እና የፖለቲካ ጉዳዮች ጋር እየተወሳሰበ የብዙዎቻችንን ሕይወት እና ወጣቱን የጥበብ ትውልድም የሚያውክ መሆኑን የምትረዱ ጥቂት አትሆኑም ብዬ እገምታለሁ። ስለዚህ እናንተም ከእኔ ጋር በየልባችሁ ሸፍታችሁ ነበር ማለት ነው። ይህ ትክክል ከሆነ ይቅርታዬን መልሼ ልወስድ ነው ማለት ነው? አይደለም። ቀልዴን ነው። እናንተም አትስትቱትም።

አሁን፣ ከዚህ መድረክ ለእናንተ ስለሚቀርበው ፕሮግራም ላስታውቅ። አንደኛው፣ ይህ እየተገባደደ ያለው የእኔ መግቢያ ነው። ሁለተኛው፣ አቶ ብርሃነ መስቀል የሚያቀርብልን የአቶ ገብረ ክርስቶስ ደስታ አጭር ታሪክ ነው። አቶ ብርሃነ መስቀል፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚገኘው የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ተማሪ ነበር። የመመረቂያ ፅሁፉን በአቶ ገብረ ክርስቶስ የሕይወት ታሪክ ላይ ሲያደርግ በሩቁ የማማከር እድል ገጥሞኝ ስለነበረ ነው ዛሬ እዚህ የጋበዝሁት። ጥናቱን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አዳብሮታል ብዬ አስባለሁ። የደረሰበትንና የወደፊት ሃሳቡን ባጭሩ ይነግረናል። ሶስተኛው፣ "ገብረ ክርስቶስ፡ ገጣሚ-ሰዓሊ? ወይስ ሰዓሊ-ገጣሚ?" የሚለው ርእስ ነው። ይህንን ከባድ ጥያቄ መነሻ አድርጎ፣ አቶ እሸቱ ጥሩነህ እንዲናገር ተወስኖ ነበር። በዝግጅት ላይ እያለ በስራ ጉዳይ ወደ ውጭ ሀገር እንዲጓዝ የሚያስገድድ አጋጣሚ መጣ። ስልክ ደውሎ ይህንን መስቀል ለታዋቂው ሰዓሊ-ቀራጭ-ገጣሚና መምህር

ለሆነው ለአቶ በቀለ መኮንን ማስተላለፉን ነገረኝ። ከአቶ በቀለ ጋር በስልክ ተነጋግረናል። በነበረው ጊዜ ያዘጋጀልንን ወቅቱን ጠብቆ ያቀርብልናል። አራተኛው ፕሮግራም፣ የግጥም ንባብ ነው። ከጠላት ዘመን ጀምሮ በታተሙት የኢትዮጵያ ጋዜጦች ላይ ባለፉት 24-25 ዓመታት የማደርገው አንድ ስነፅሁፍ-ቀመስ ጥናት አለ። ታድያ፣ አንዳንዴ፣ አንዳንድ ቀልቤን የሚስቡ ነገሮችንም በጎን እከታተል ነበር። የአቶ ገብረክርስቶስ ግጥሞችና ጽሁፎች ከእነዚህ ቀልብ-ሳቢዎቼ መሀል ነበሩ። በእጄ ያሉትን አንባብያን እጅ ለማድረስ እየፈለግሁ እስከዛሬ ሳልችል ቀረሁ። በቅርቡ ቀደምት ድርሰቶችን እና የአንዳንድ ታዋቂ ደራስያንን ስራ የማሳተምን ቁምነገር የሚያበረታታ መልካም ዜና ከሚታመን ምንጭ ሰምቻለሁ። ዜናው ተግባር ሲሆን፣ የአቶ ገብረ ክርስቶስን ግጥሞችና በጋዜጣ የወጡትን ጽሑፎቹን፣ አቶ እሸቱ ስለእርሱ ስራዎች ያዘጋጀውን ጽሁፍ፣ የአቶ ብርሃነመስቀልን ጽሁፍ እና ሌሎች እኛ ያላገኘናቸውን ጥናቶችና ምንጮች አጠናቅሮ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ በኩል የሚገባውን ማእረግ ይዞ እንዲታተም ጥረት እናደርጋለን። በስሙ ቋሚ ኤግዚቢሽን እንደሚዘጋጅ ከተለያዩ ምንጮች እየተነገረ ስለሆነ፣ የመጽሐፉ ታትሞ መውጣት ከኢግዚቢሽኑ ቦታ መመረቅ ጋር እንዲገጥምም ተጨማሪ ጥረት ይደረጋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እስከዚያው፣ ከሰበሰብኳቸው ግጥሞች አንዳንዶቹን አሰማችኋለሁ። የአቶ ገብረ ክርስቶስን አነባበብ ግን ልከተል አልችልም። የቻለ ሰው እስከዛሬ አላጋጠመኝም። የእርሱ አነባበብ በጣም ልዩ ይመስለኛል[1]። በባህል ላይ ያወጀው፣ ጮክ ብሎ የሚደመጥ፣ ልዩ የአካል እና የመንፈስ ነፃነት እና ያንንም የሚገልፅበት የተለየ ስልት የነበረው ገጣሚ ነበር ብዬ የምር አምናለሁ። እንዲህ ደፍሬ የምናገረው፣ እኔ፣ እስከዛሬ፣ አንድም ቀን፣ ግጥሞቼን ሙሉ በሙሉ ነፍስያዬ ወይም የእኔ የብቻዬ እኔ እንደሚፈልገው በአደባባይ አንብቤያለሁ ብዬ ስለማላምን እና ምክንያቱም ምን እንደሆነ ስለማውቅ ይመስለኛል።

ከዚህ ወደናንተ የሚቀርቡት ፕሮግራሞች እነዚህ ናቸው። ከእናንተ ከአድማጮቻችን በኩል ደግሞ፦

አንደኛ፦ አቶ ገብረ ክርስቶስንና ስራውን በቅርብ የሚያውቁ የመሰሉኝን አምስት ሰዎች ጋብዤ፣ እያንዳንዳቸው በሶስት በሶስት ደቂቃ ውስጥ ዋና ዋና ቁምነገሮችን እንዲናገሩ እንዳደርግ እንድትፈቅዱልኝ፤

---

[1] ለነገሩ የያንዳንዱ ገጣሚ አነባበብ ልዩ ነው። እስቲ የአቶ ሰይፉ መታፈሪያን፣ የአቶ መንግስቱ ለማን የአቶ ፀጋዬ ገብረ መድኅንን፣ የአቶ ሰሎሞን ዴሬሳን እና  የምታውቋቸውን ሌሎች ገጣምያን አነባበብ በምናባችሁ ለማነፃፀር ሞክሩ። በበኩሌ፣ አንዳንዶቹን ግጥሞቼን የማነብና የምከውንበት ሁኔታ በወቅቱ ባለሁበት የስነልቡና እና የመንፈስ ሁኔታ፤ እንደማነብበት ቦታ ድባብ፣ እንደ እለቱ የአየር ሁኔታ፣ እንደ አድማጭ-ተመልካቹ እድሜ እና ተሳትፎ ወዘተ. በየጊዜው ሲለዋወጥ አስተውያለሁ።

ሁለተኛ፥ እናንተ እጅ እያወጣችሁ፥ እኔ እንደተለመደው በብድግ-ብድግ እድል እየሰጠኋችሁ ውይይቱ እንዲቀጥል እንድትተባበሩኝ ሃሳብ አቀርባለሁ።

በመጨረሻ፥ የዛሬው ፕሮግራም የገብረክርስቶስ ስለሆነ፣ በተቻለን መጠን፥

1ኛ- ስለ ሕይወት ፍልስፍናው፥ ስለመምህርነቱ እና ስለ እለት ተእለት ኑሮው የሚናገሩ የግል ገጠመኞችን፥ ወጎችን፥ እና ጽሁፎችን እያነሳን ስለ ሰብእናው ብንወያይ፣

2ኛ- የሰውዬውን የስእል ስራዎች ምንነት እያወሳን፥ በአፍሪካና በዓለም አላቸው የሚባለውን ስፍራ እየጠቀስን ብናወጋ፣

3ኛ- ግጥሞቹ እና ሌሎች ድርሰቶቹ በሀገሪቱ የግጥምና የድርሰት ታሪክ ውስጥ ያላቸውን ስፍራ እያነሳን ብንወያይ ጠቃሚ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ!

---

ጥቅምት 10/1996 ተጻፈ፣ ጥቅምት 12-1996 እየታደተ ("edit ተደረገ" ለማለት) ተተየበ፣ ጥር 21 1998 በመጠኑ ታደተ።